ספריית פיג'מה

## ሻልኬቱ - המשך פעילויות בעקבות הסיפור




በ: ዮራም ዔበር-ሃዳኒ
ምሳሌዎች: ናዓማ ጎሎምብ
הוֹצָאָה: ספרית פועלים
የእድሜ ክልል: መዋዕለ ሕጻናት

שִׂיחָה

**ምርጥ ስሜት መሰማት**

ሻልኬት ምርጥ ስሜት እንዲሰማው የሚያደርገውን መንገድ አግንቷል። ምርጥ ስሜት ማለት ምን ማለት ነው? በዚህ ጉዳይ ላይ መወያየትና መጠየቅ ይችላሉ – ሻልኬት እንደዚህ እንዲሰማው ያደረገው ምንድን ነው? መቼ ነው ?እንደዚህ ዓይነት ስሜት የሚሰማን? ምንስ ይረዳናል

לָצֵאת הַחוּצָה

**በአካባቢያችን ያለውን ውበት ማየት**

በአካባቢዎ የእግር ጉዞ ማድረግና የተደበቀን ውበት ለማግኘት መሞከር ይችላሉ። እንደ ቅጠል ወይም ድንጋይ ባሉ አንድ ቀላል ነገር ላይ በማተኮር እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ለመታዘብ የመረጠውን የሚገልጽበትን ጨዋታ መጫወት ይችላል። አንድ ዛፍ ወይም ቁጥቋጦ መምረጥና ወቅቶች ሲቀየሩ ምን እንደሚፈጠር ማየት ይችላሉ።

יְצִירָה

**ትንሽ ቀለም ማስገባት**

በመጽሐፉ ውስጥ ባሉት ምስሎች አነሳሽነት በቤት ውስጥ መሳል ይችላሉ። በመጀመሪያ ቅጠሎችን ይሰብስቡና ከእነርሡ ውስጥ አንድ ቅጠል ይምረጡ። ብሩሽ በመጠቀም ቅጠሉን በባለ ውሃ ቀለም ማስቲካ ይቀቡ። ከዚያም ወደ ነጭ ሉክ ያያይዙት። ቀለሙ ከደረቀ በኋላ ስዕሉን በማርከር ወይም በጥቁር እስክርቢቶ መቀጠል ይችላሉ።

חֵקֶר

**የቅጠል ቅርንጫፍ**

ሥር ሊሰድዱ የሚችሉ የእጽዋት ቅጠሎች አሉ — ከግንዱ አጠገብ ያለውን የቅጠል ጫፍ በመትከል እርጥብ ዓፈር ባለው ማሰሮ ውስጥ አድርገው አዲስ ተክል ያብቅሉ። ይህንን መሞከር ይችላሉ፡- ለምሣሌ፡- በሳንሴቪዬሪያ ተክል፣ በፔፔሮሚያ ቅጠል ወይም በተለያዩ ድርቅን የሚቋቋሙ የበረሃ ተክል ቅጠሎች።

סִרְטוֹנִים

**QR ኮድ**

ኮዱን ስካን ያድርጉና ‘ሃሻልኬት’ በተሰኘው የናዓማ ጎሎምብ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ሥዕላዊ መግለጫዎች አነሳሽነት ልዩ ልዩ የፈጠራ እድሎችን በቅጠሎች ይስሩ።

הַשְׁרָאָה

**ፒንተረስት**

[ተጨማሪ ሥራዎችን፣ ግጥሞችንና እንቅስቃሴዎችን በፒጃማ ቤተ መፃህፍት ፒንተረስት ላይ]()

עוד פעילויות באתר ספריית פיג'מה www.pjisrael.org